# እውነተኛው አምላክ ማነው?

(መጽሐፍ ቅዱስንና ቅዱስ ቁርዓንን መሠረት ያደረገ ምላሽ)

አዘጋጅ፦ ዑመር አርሲ

ሰኔ 2017

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

መግቢያ .................................................... 3

እውነተኛው አምላክ በአዲስ ኪዳን ................ 5

እውነተኛው አምላክ በብሉይ ኪዳን............. 10

ኢየሱስ ብቻ ነው ጌታ የተባለዉ? ------------- 12

እውነተኛው አምላክ በቅዱስ ቁርዓን…………..13

እውን ኢየሱስ ተሰቅሏልን? ..................... 16

የመልዕክቱ ማጠቃለያ...............................18

# መግቢያ

## በአላህ ስም፤ እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

በቅድሚያ ይህችን መልዕክት ለማዘጋጀት ያስቻለኝን ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርዓን ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ስለመሆናቸው አንዱ ማረጋገጫችን ከበቂ በላይ የሆኑ ተመሳሳይነት ያላቸው መልዕክቶች በሁለቱም ውስጥ መገኘታቸው ነዉ፡፡ ሁለቱ ቅዱሳን መፅሀፍት ለሰዎች ቀናን መንገድ እንዲያስተምሩ ከኃያሉ አምላካችን የተላኩ መለኮታዊ መመሪያዎች ናቸው እንጂ በድንገት የወረዱ አይደሉም፡፡ በእርግጥ ቅዱስ ቁርዓን የሙስሊሞች ብቸኛው መለኮታዊ መርህ መሆኑ አጠራጣሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ መልዕክት ውስጥ እንግዳ ሊሆን የሚችል ነገር ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዊ ጠቀሜታው ከክርስቲያኖች ይልቅ ለሙስሊሞች ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አለመሆኑ ነው፡፡

አንዳንድ የሙስሊም ፀሐፊዎች አሉታዊ ገጽታ ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በመዳሰስ ብቻ መጽሐፉ መለኮታዊ አይደለም ብሎ ይደመድማሉ፡፡ እኔ ግን አዎንታዊ ገጽታ ያላቸዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ከክርስቲያኖች ይልቅ ለሙስሊሞች የሚጠቅሙ ሆኖ ስላገኘኋቸው ለመጽሐፍ ቅደስ ያለኝ አክብሮት ምን ጊዜም በልቤ ውስጥ ተቀርጾ ይኖራል፡፡ምክንያቱም ከክርስትና እምነት ወደ እስልምና የመጡት ምሁራን በተደጋጋሚ ሲናገሩ እንደተደመጡት ወደ እስልምና ለመመለሳቸው መሠረታዊ ምክንያታቸው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን ጌትነት የማይቀበል ከሆነ፣ ኢየሱስን የሰው ልጅ ብሎ የሚጠራ ከሆነ፣ ኢየሱስ ለእስራኤል ወገኖች ብቻ የተላከ ነብይ ብሎ ከደነገገና የኢየሱስን አላመሰቀል ካረጋገጠ ከቅዱስ ቁርኣን የሚለይበት የጎላ ምክንያት ስለሌለዉ የሙስሊሞች የመረጃቸው ሀብት ሊሆን ይችላል፡፡

የቅዱስ ቁርኣንና የመጽሐፍ ቅዱስን መለኮታዊነት አስመልክቶ ኃያሉ አምላካችን አላህ በተከበረዉ ቃሉ ሁለቱ ቅዱሳን መጻሕፍት ብርሃንና ገላጭ መሆናቸውን በሚከተሉት አንቀጾች ይገልፃል፡፡

1/ ‹‹እኛ ተዉራትን በዉስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፡፡›› (አል-ማኢዳ 5 ፡44)

2/ ‹‹በፈለጎቻቸዉም (በነቢያቱ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተዉራት በስተፊቱ ያለዉን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጂልንም በዉስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት፣ ከበስተፊቱ ያለችዉን ተዉራትንም የሚያረጋግጥ፣ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነዉ፡፡›› (አል-ማኢዳ 5 ፡46)

3/ ‹‹ወደአንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለዉን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በእዉነት አወረድን፡፡›› (አል- ማኢዳ 5 ፡48)

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሙስሊሞች መለኮታዊ መጽሐፍ የሆነው ቅዱስ ቁርኣን ለመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤቶች የሚከተከለውን ጥሪ ያደርጋል፡-

‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለናንተ የሚገልጽ፣ ከብዙውም የሚተው ሲሆን መልዕክተኛችን (ሙሐመድ) በርግጥ መጣላችሁ፡፡ ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡›› (አል-ማኢዳ 5፡15)

***

# እዉነተኛው አምላክ በአዲስ ኪዳን

1/ ‹‹ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፡- ‹አባት ሆይ! የሰማይና የምድር ጌታ ሆይ! ...›› *(የማቴ. ወንጌሌ 11፡ 25)* ምናልባትም ኢየሱስ ጌታም ባይሆን የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል፡፡ ‹‹ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ፡፡›› *(የዮሐ. ወንጌል 20፡ 17)* ‹‹አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ፡፡›› *(የማቴምስ ወንጌል 23 ፡9)*

ስለዚህ በኢየሱስ ትምህርት መሠረት እግዚአብሔር የርሱ አባት ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ዘር አባት ነው፡፡ከዚህም የምንማራቸው ቁም ነገሮች፡-

ሀ) የሰማዩና የምድሩ ጌታ ኢየሱስ አለመሆኑን፣

ለ) ፈጣሪ የኢየሱስ አባትና አምላክ እንደሆነ ሁሉ ለኛም አባታችንና አምላካችን ነዉ፡፡

2/ ታዲያ ‹‹ኢየሱስ ምን ሊሆን ነው?›› ለሚለው ጥያቄ መልሱ ‹‹የሰው ልጅና ብርቱ ነቢይ ነው›› የሚለው ይሆናል፡፡

ሀ) ‹‹አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔር እና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡›› (1 ኛ ጢሞቴዎስ *2 ፡5)*

ለ) ‹‹በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነብይ ...›› *(የሉቃስ ወንጌሌ 24፡ 19-21)*

ሐ)‹‹የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቷልና ...›› *(ሉቃስ 7፡34)*

መ) ‹ሕኔ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም፡፡›› *( ማቴዎስ 15፡24)*

3/ እውን ኢየሱስና እግዚአብሔር አብ እኩል ናቸውን? እኩል አይደሉም! ‹‹ከኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፡፡›› *(የዮሐ. ወንጌል 14 ፡28)*

4/ በኢየሱስ ትምህርት መሠረት እውነተኛው አምላክ ማነው?

ሀ) ‹‹እውነተኛ አምላክ የሆንክ አንተ ብቻ! ...›› *(የዮሐ. ወንጌል 17፡3)*

ለ) ‹‹እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም አርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት፡፡›› *(የዮሐንስ ወንጌል 20፡17)*

ሐ) ‹‹እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፡፡›› *(የዮሐንስ ወንጌል 5፡30-32)*

መ) ‹‹እኔም በራሴ አልመጣሁም፤ ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው፡፡›› *(የዮሐ. ወንጌል 7፡28)*

5/ ኢየሱስን ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉት የት ሊገቡ ነው?

‹‹በሰማያት ያለውን የአባቴን ፍቃድ የሚያደርግ እንጂ ‹ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ!› የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡›› *(የማቴ. ወንጌል 7፡ 21-23)*

6/ ከትዕዛዛት ሁሉ የመጀመሪዪቱ ማን ናት? ‹‹እስራኤል ሆይ ስማ! ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፡፡ ›› (ማርቆስ *12፡29)*

7/ ሦስቱ የሥላሴ አካላት እኩል ሥልጣን አላቸውን? እኩል ሥልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ሦስቱም የመጨረሻውን ቀንና ሰዓት ባወቁ ነበር፡፡ ነገር ግን ‹‹ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን

የሚያውቅ የለም፡፡›› *(የማቴ ወንጌል 24፡36)* ታዲያ ሁለቱ የተቀሩት አምላክ ከሆኑ ለምን አላወቁም?

8/ ‹‹ኢየሱስ፡- ‹ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎዋል አለው፡፡›› *(የማቴ ወንጌል 4፡10)*

9/ ‹‹የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ፡፡›› (*1ኛ ቆሮንቶስ 11፡3)*

10/ ‹‹አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፡፡›› *(የዮሐንስ ወንጌል 10፡29)* ይህ ማለት ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስም ይበልጣል ማለት ነዉ፡፡

11/ ‹‹አንድ አምላክ አብ አለን፡፡›› *(1ኛ ቆሮ 8፡6)* ወልድና መንፈስ ቅዱስስ አምላኮች አይደለምን?

12/ ‹‹የተባረከውና ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያሳየው ነው፡፡ እርሱ ብቻ የማይሞት፣ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም፡፡›› *(1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16)* ስለዚህ ኢየሱስ በሰዎች ታይቷልና አምላክ አይደለም፡፡

13/ ኢየሱስ እራሱ እግዚአብሔርን የሚገዛ መሆኑን እንመልከት፡-

‹‹ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልድ፣ እራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛ ለርሱ ይገዛል፡፡›› *(1ኛ ቆሮንቶስ 15፡28)*

14/ ‹‹ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋና ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክቡር እስከ ዘለዓለም ድረስ ይሁን፤ አሜን፡፡›› *(1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17)*

15/ ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እኩል የአምላክነት ሥልጣን አላቸው፡ በተለይም በመጨረሻው የፍርድ ቀን ኢየሱስ ለፍርድ እንደሚመጣ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን ሐሳብ አይደግፍም፡፡ ኢየሱስም ከፈጣሪ ጋር ምንም ሥልጣን አይጋራም፡፡

- ሀ. አብ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ እላይ ዮሐ. 14፡28 ተመልክተናል፡፡
- ለ. ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም - (የዮሐንስ ወንጌል 5፡14)
- ሐ. ኢየሱስ እርሱን ‹ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ› በሚሉት ላይ ዓመፀኞች ብሎ እንደሚመሰክርባቸው ከላይ አይተናል - (ማቴ 7፡21-23)፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ መስካሪ እንጂ ፈራጅ አይሆንም ማለት ነው፡፡
- መ. በፍጻሜ ቀን መንግስትን ለእግዚአብሔር አብ እንደሚያስረክብ (1ኛ ቆሮ 15፡22-24) እንመልከት፡፡

***

# እውነተኛው አምላክ በብሉይ ኪዳን

1/ ‹‹እኔ አምላክ ነኝና ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም፡፡›› (ኢሳያስ 46፡9)

2/ ‹‹እግዚአብሔር ከኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤ ከእኔም በኃላ አይሆንም፤ እኔ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከኔ ሌላም የሚያድን የለም› አለ፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 43፡10-11)* ‹‹ኢየሱስ ያድናል›› የሚለው የክርስቲያኖች እምነት በዚህ ጥቅስ መሠረት ተቀባይነት የለውም፡፡

3/ ‹‹እኔ ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኃለኛ ነኝ፤ ከኔ ሌላም አምላክ የለም፤ እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሳና ይጥራ ይናገር፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 44፡6)*

4/ ‹‹ሁሉን የፈጠርሁ፣ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፣ ምድርንም ያፀናው እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማን ነበር?› *(ትንቢተ ኢሳ 44፡24)*

5/ ‹‹ከኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም፤ ማንንም አላውቅም፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 44፡8)*

6/ ‹‹ከኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፤ ከኔም በቀር ማንም የለም፤ እኔ አምላክ ነኝና ከኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ፤

ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 45፡21-23)* ‹‹እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ፡፡›› *(2 ኤፌሶን 3፡14)*

7/ ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን ዉስጥ ያለዉን የፈጣሪን አንድነት ቸል የሚሉት የኦሪት ሕግ ተሽሯል በማለት ነዉ፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ሕግጋትንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣሁም፤ ለመፈፀም እንጂ፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ ቀንሶ ለሰው የሚያስተምር እርሱ በመንግስተ ሰማይ ታናሽ ይባላል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ትዕዛዛት እየፈጸመ ሌሎችን እንዲፈጽሙ የሚያስተምር እርሱ በመንግስተ ሰማይ ታላቅ ይባላል፡፡›› *(ማቴ 5፡17-19)* ስለዚህ የኦሪት ሕግ ዘለዓለም አይሻርም ማለት ነዉ፡፡ ለዚህም ነው ቁርኣን የወረደው፡፡

8/ ክርስቲያኖች ሲያስተምሩ ‹‹አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስትም ናቸው አንድም ናቸው!›› ይላሉ፡፡ እንዴት ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ሚስጥረ ሥላሴ ለሰው አይገባም!›› ይላሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በሚከተሉት ጥቅሶች ሚስጥራዊ አምላክ እንደሌለ ያጋልጣል፡፡

*ሀ.* ‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከኔም በቀር ሌላ የለም፤ በስውር ወይም በጨለማ ስፍራ አልተናገርኩም፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 45፡19)*

ለ. ኢየሱስ ደግሞ ሲናገር፡- ‹‹እንግዲህ አትፍራቸው፤ የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለምና፡፡›› *(ማቴ. 10፡26)*

ሐ. ‹‹ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል፡፡›› *(ማቴ. 10፡42)* ስለዚህ ነቢይን ከነቢይ በላይ ከፍ በማድረግ ከፈጣሪ ጋር ማምለክ የነቢይን ዋጋ ያሳጣል ማለት ነው፡፡

9/ ‹‹ክርክራችሁን አቅርቡ፤ ማስረጃችሁን አምጡ ይላል እግዚአብሔር፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 41፡21)*

10/ ‹‹ሕዝቤ ሆይ! መሪዎችህ አሳስተውሃል፤ ከመንገድም መልሰውሃል፡፡›› *(ትንቢተ ኢሳያስ 3 ፡12)*

11/ ‹‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል፡፡›› *(ሆሴዕ 4፡6)*

12/ ‹‹እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና በቁጣ አልመጣሁም፡፡›› *(ሆሴዕ 11፡9)* አሁንም ‹‹ኢየሱስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው›› የሚለው እምነት በዚህ ጥቅስ መሠረት ተቀባይነት የለውም፤ ምክንያቱም አምላክ ሰው አይደለምና፡፡

13/ ‹‹ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ አግዚአብሔር አምላክ እኔ ነኝ፤ ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡፡›› *(ዘዳግም 5፡ 6-7)*

## ኢየሱስ ብቻ ነው ጌታ የተባለው?

- አብረሃም፡ ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሏል። ኦሪት ዘፍጥረት 18፡12
- ኤልያስ፡ አብድዩም በመንገድ ሲሄድ እነሆ ኤልያስ ተገናኘዉ። አብድዩም አወቀዉ በግንባሩም ተደፍቶ ጌታዬ ሆይ ኤልያስ አንተ ነህን? አለ። 1ኛ ነገስት 18፡7
- ኤልሳዕ፡ የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕ እነሆ ጌታችን እንደምታይ የዚህች ከተማ ኑሮ መልካም ነዉ ዉሃዉ ግን ክፉ ነዉ ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት። 2ኛ ነገስት 2፡19
- ሙሴ፡ አሮንም፦ ጌታዬ ሆይ ቁጣህ አይቃጠል፤ይህ ህዝብ ክፋትን እንደወደደ አንተ ታዉቃለህ። ኦሪት ዘፀአት 32፡22
- ዮሴፍ፡ እነርሱም አሉት ጌታችን ሆይ አይደለም ባርያዎችህ ስንዴን ሊገዙ መጥተዋል። ኦሪት ዘፍጥረት 42፡10

ስለዚህ ጌታ የተባሉት ሰዎች ሁሉ አምላክ ከሆኑ ስንት አምላኮች አሉ? መፅሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ኢየሱስም ጌታ ነዉ የተባለዉ እንጂ አምላክ አልተባለም ጌታና አምላክ አንድ አይደሉም።

የሚከተለዉ የመጽሀፍ ቅዱስ አንቀጽ ጌታና አምላክን ለይቶ ያስተምራል።

ለኛስ ነገር ሁሉ ከርሱ የሆነ እኛም ለርሱ የሆነን አንድ አምላክ አብ አለን። ነገር ሁሉ በርሱ በኩል የሆነ እኛም በርሱ በኩል የሆነን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። 1ኛ ቆሮ 8፡6
መንፈስ ቅዱስስ ተረሳ?
በመጨረሻም ለክርስቲያኖች የቤት ሥራ የሚሆኑትን ጥያቄዎች እንጠይቃለን።

አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ። ኤፌሶን 4፡5-6

- አንድ ሃይማኖት የትኛዉ ነዉ? ኦርቶዶክስ? ፕሮቴስታንት? ወይንስ ካቶሊክ?
- ኢየሱስ፡ ጌታ ነዉ ወይንስ፡ አምላክ? ‹‹ሐዋሪያቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።›› የሐዋ ሥራ 11፡26

የኢየሱስና የሐዋሪየቶች ኃይማኖት ኢየሱስ በሚያስተምርበት ወቅቶች ምን ነበር? ምክንያቱም ኢየሱስ፡ ወደ ሰማይ ከወጣ በኃላ ነዉ ሐዋሪያቶቹ ክርስቲያን ተብለዉ የተሰየሙት።
ኢየሱስ ጌታ የሚሆነዉ፡ ወደ ሰማይ ስለወጣ ነዉ ለሚሉት፡ መልሱ ሄኖክም ወደ ሰማይ ወጣ ኦሪት ዘፍጥረት 5፡24 ኤልያስም በአዉሎ ንፋስ፡ ወደ፡ ሰማይ ወጣ 2ኛ ነገስት 2፡11
ሌላዉ ምክንያት ደግሞ ሙታን ስላነሳ ነዉ፡ ጌታ የሚሆነዉ፡ ለሚሉት መልሱ ኤልያስ የሞተዉን ሰዉ ቀስቅሷል። 1ኛ ነገስት 17፡22 ኤልሳዕ በ2ኛ ነገስት፡ 4፡34 የሞተዉን ሰዉ አስነስቷል። ስለዚህ ወደ ሰማይ መዉጣት እና ሙታንን መቀስቀስ ጌታ የሚያሰኝ ከሆነ ሄኖክ ኤልያስና ኤልሳዕም ጌቶች ናቸዉ ማለት ነዉ?
ክርስቲያኖች ኢየሱስ ፍጹም፡ ሰዉ ፍጹም አምላክ ነዉ ይላሉ ይህም በ451 በቀልኪዳን ጉባኤ የተደነገገ እንጂ በምንም፡ መልኩ፡ እግዚአብሔር ሰዉ እንደማይሆን መጽሀፍ ቅዱስ ያስተምራል።
ሀሰት ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰዉ አይደለም ይጸጸትም ዘንድ እግዚአብሔር የሰዉ ልጅ አይደለም ኦሪት ዘኁልቅ 23፡19
ሠ. የርህራሄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። 2ኛ ቆሮ 1፡3

‹‹ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ።›› ዮሐንስ 20፡17 ይህም ማለት እግዚአብሔር የሁሉም አባትና አምላክ እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ብቻ አይደለም። የመልክቱ መደምደምያ ግን ኢየሱስ አምላክ እንዳልሆነ እና የራሱ አምላክ ግን እንዳለዉ ዓለም እንዲገነዘብ ነዉ።

1. እግዚአብሔር፡ የጻፈለችሁንም ስርዓትና ፍርድ ህግና ትዕዛዝም ለዘለዓለም ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ፤ ሌሎችንም አማልክት አትፍሩ። 2ኛ ነገስት 17፡37
2. እግዚአብሔር የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ በቤት የተወለደ ወይም ከዘራችሁ ያይደለ በብርም ከእንግዳ ሰዉ የተገዛ ወንድ ሁሉ በትውልዳችሁ ይገረዝ በቤትህ የተወለደ በብርም የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ ቃል ኪዳኔም በስጋችሁ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ይሆናል የቁልፈቱን ስጋ ያልተገረዘ ቁላፍ ሰዉ ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና። ኦሪት ዘፍጥረት 17፡12-14
3. ኢየሱስ፡ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትዕዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰዉም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰዉ በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል። ማቲዎስ 5፡19
4. ጳዉሎስ ከእግዚአብሔርና ከኢየሱስ ይበልጣልን? ምን ያህልስ ደፋር ነዉ? ህጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትዕዛዝ ተሽራለች። ዕብራውያን 7፡18-19
5. ጳዉሎስ፡ እነሆ እኔ ጳዉሎስ እለችኃለሁ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም በህግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋዉ ወድቃችኃል። ገላቲያስ 5፡1-6 እላይ በ2 እና በ 3 ቁጥር ከተጠቀሱት ጋር የሚጋጭ ትምህርት ጳዉሎስ ከማን ተምሮ ነዉ የሚያስተምረዉ? እግዚአብሔርና ኢየሱስ ያላስተማሩትን?
6. ጳዉሎስ፡ ሰዉ ያለ ህግ ስራ በዕምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። ሮሜ 3፡28 እላይ በ3 ቁጥር የተጠቀሰዉንና ቀጥሎ በ7 ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉን ስናገናዝብ ጳዉሎስ ምን አይነት ሰዉ እንደ ሆነ መረዳት ይቻላል።
7. ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነዉ እናዉቃለን አውቄዋለዉ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ዉሸተኛ ነዉ እዉነትም በርሱ ዉስጥ የለም። 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 2፡3-4 አንተ ከንቱ ሰዉ እምነት ከስራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታዉቅ ትወዳለህን? የያዕቆብ መልዕክት 2፡20 ሁለቱ ሐዋሪያት ዮሐንስና ያዕቆብ የጳዉሎስ አይነት ትምህርት የሚያስተምር ሰዉ ከንቱና ዉሸተኛ ነዉ ይላሉ።
8. ጳዉሎስ በራሱ ላይ እንደሚከተለዉ ሲመሰክር ተመልከቱ፡- ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነትን እንዳልታበይ የሥጋዬ መዉግያ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልዕክተኛ ተሰጠኝ። ይኸዉም እንዳልታበይ ነዉ። 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 ምናልባት ከንቱ እና ዉሸተኛ የሚያሰኝ ሥራ የሰራዉ በተሰጠዉ የሰይጣን መልዕክተኛ ይሆን ይሁን?
9. ጳዉሎስ፡ ስለድንግልም የጌታ ትዕዛዝ፡ የለኝም ነገር ግን የታመንሁ እሆን ዘንድ ከጌታ ምህረት የተቀበልሁ እንደመሆኔ ምክር እመክራለሁ። 1ኛ ቆሮንቶስ 7፡25 ጳዉሎስ፡ ከ12 ሐዋሪያት ዉጭ ሆኖ እንዴት ሆኖ የታመነ ሊሆን ይችላል ዮሐንስና ያዕቆብ ዉሸተኛ እና ከንቱ እያሉት? ይባስ ኢየሱስ በመንግስተ ሰማያት ታናሽ ነዉ ብሎታል በማቴዎስ 5፡19 ህግን በመሻር ለሰዉ የሚያስተምር በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ማንም ሰዉ የለም ከጳዉሎስ በስተቀር። በስም ጠቅሰዉ ጳዉሎስ አላለዉም እንጂ ማቴዎስ 5፡19 እርሱን፡ ይመለከታል። ሥራ የሌለዉ ዕምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነዉ። የያዕቆብ መልዕክት 2፡17

10 ጳዉሎስ አንድ ቀን ወደ ደማስቆ እየሄደ እያለ ብርሃን መጣበት እና

1ኛ ሁላችን ወደቅን የሐዋሪያት ሥራ 26፡9-20

2ኛ ጳዉሎስ ብቻዉን ወድቆ ሌሎች ቆሙ ድምፅ ሰሙ እንጂ ብርሃኑን አላዩም የሐዋ ሥራ 9፡1- 3ኛ ከርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ብርሃኑን አዩ እንጂ ድምጹን አልሰሙም። የሐዋ ሥራ 22፡6-11

## እውነተኛው አምላክ በቅዱስ ቁርኣን

1/ ‹‹እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ ዒሳ መሲሕ ነው ያሉ በርግጥ ካዱ፡፡ አል-መሲሕም አለ፡- ‹የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤ እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበደዮች ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡›› *(ሱረቱል ማኢዳ 5፡72)* ይህንንም ከዮሐንስ ወንጌል 20፡17 ጋር እናዛምድ፡፡

2/ ‹‹በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ለአላህ አሞገሰ፤ እርሱም ሁሉን አሸናፊ ጥበበኛው ነው፡፡ የሰማያትና የምድር ንግሥና የርሱ ብቻ ነው፡፡ ሕያው ያደርጋል፤ ይገድላል፡፡ እርሱም ነገሩን ሁሉ ቻይ ነው፡፡ እርሱ ፊትም ያለ ኋላም ቀሪ ግልጽም ስውርም ነው፡፡ እርሱም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው፡፡ ›› *(አል- ሐዲድ 57፡1-3)* አሁንም በብለይ ኪዳን ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ጥቅስ አለ፡፡ ‹‹እኔ ብቻዬን እንደሆንሁ፣ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፡፡ እኔ እገላለሁ፤ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፤ እፈውሳማለሁ፤ ከእጄም የሚድን የለም፡፡›› *(ዘዳግም 32፡39)*

3/ ‹‹እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክ አንድ አምላክ እንጂ ሌላ የለም፡፡ ከሚሉት ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያ የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በርግጥ ይነካቸዋል፡፡*(አል-ማኢዳ 5፡73)*

4/ ‹‹አላህም አለ፡- ‹ሁለት አማልክት አትያዙ፤ እርሱ አንድ አምላክ ብቻ ነውና፡፡ እኔንም ብቻ ፍሩ፡፡›› *(አን-ነሕል 16፡51)*

5/ ‹‹የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ከበፊት መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፈ የሆነ መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ ሁለቱም ምግብን የሚበሉ ነበሩ፡፡ አንቀጾችን ለነሱ *(ለከሐዲዎች)* እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፡፡ ከዚያም ከእውነት እንዴት እንሚመለሱ ተመልከት፡፡›› *(አል-ማኢዳህ 5፡75)*

6/ ‹‹እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፡፡ የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት *(የይሁን)* ቃሉም፣ ከርሱ የሆነ መንፈስን ብቻ ነው፡፡ በአላህና በመልዕክተኞቹ እመኑ፡፡ *(አማልክት)* ሦስት ናቸው አትበሉ፤ ተከልከሉ፡፡ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፡፡ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው፡፡ መመኪያም በአላህ በቃ፡፡›› *(አን-ኒሳእ 4 ፡171)*

7/ ‹‹የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከነሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም፡- ‹በዚያ ወደኛ በተወረደ፣ ወደናንተም በተወረደው አመንን፤ አምላካችንም አምላካችሁ አንድ ነው፤ እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን፡፡›› *(አል-ዐንከቡት 29፡46)*

8/ ‹‹በል እርሱ አላህ አንድ ነው፡፡ አላህ የሁሉም መጠጊያ ነው፡፡ አልወለደም፤ አልተወለደምም፤ ለእርሱ አንድም ቢጤ የለውም፡፡›› *(አል-ኢኽላስ 112፡1-4)*

9/ ‹‹ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? እውነተኞች እንደሆናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው፡፡›› *(ሱረቱ ነምል 27፡64)* ከላይ ከተጠቀሰው ኢሳይያስ 41፡21 ጋር አንድ ነው፡፡

10/ ‹‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎች እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? አላህ በሚለው ጊዜ አስታውስ፡፡ ‹ጥራት ይገባህ፤ ተገቢዬ ያልሆነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፤ ብዬውም እንደሆነም በርግጥ አውቀኸዋል፤ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፤ ሩቆችን ሁሉ በጣም አዋቂ አንተ ብቻ ነህና፡፡ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም፡፡›› *(አል-ማኢዲህ 5፡116-117)*

## እዉን ኢየሱስ ተሰቅሏልን?

ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሚሆነዉ በቅርቡ በቱርክ አገር የተገኘዉ አሮጌዉ መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሳይሰቀል በሕይወት ወደ ሰማይ ያረገ መሆኑንና በምትኩ ይሁዳ መሰቀሉን ያጋልጣል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በስተመጨረሻ ነቢዩ ሙሐመድ (ዐ.ሰ.ወ) ይመጣል ብሎ ይመሰክራል፡፡ ታዲያ ይህ መጽሐፍ የት ነዉ የሚገኘዉ? ከተባለ እርስዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አንባቢ ከሆኑ መጽሐፉ በእጅዎ ይገኛል፡፡ እንዴት? …

‹‹1500 years old Bible confirms that Jesus was not crucified Vatican in awe.›› ብለው በመፃፍ ጎግል (google) ይግቡና ያንብቡ፡፡ ከዚያም የሚከተለዉን የቅዱስ ቁርኣን አንቀጽ በጥሞና ይመርምሩ፡-

‹‹እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አል-መሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸዉ ረገምናቸዉ፡፡ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፡፡ ግን ለነሱ *(የተገደለዉ ሰዉ ከዒሳ)* ተመሰለ፡፡ እነዚያም በርሱ ነገር የተለዩት ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትም፡፡ ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳዉ፤ አላህም ጥበበኛ ነዉ፡፡›› (አን-ኒሳእ *4 ፡157-158)* በኢየሱስ ምትክ ይሁዳ ነዉ የተሰቀለዉ የሚለዉ ጉዳይ አሁን ባለዉ መጽሐፍ ቅዱስም ዉስጥ ፍንጭ አለዉ፡፡

"በርሱ ነገር የተለዩት ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር" የሚለው የቁርዓን ገለፃ በመፅሀፍ ቅዱስ ሲረጋገጥ

1/ ጥርጣሬ በሰቀሉትም ጊዜ 3፡00 ሰዓት ነበር፡፡ ማርቆስ 15፡25 ጧዋት 3፡00 ሰዓት የተሰቀለው ሰው በ9፡00 ሰዓት ኤሎሄ ኤሎሄ ብሎ ጮሄ፡፡ ማርቆስ 15፡34፡፡ ሌላው ጥርጣሬ በ3፡00 ሰዓት ተሰቅሎ በ9፡00 ሰዓት የጮሄው ሰው በ6፡00 ሰዓት ለፍርድ ቀረበ፡፡ ዮሃንስ 19፡14

2/ ሁለተኛ ጥርጣሬ ‹‹ይሁዳ ብሩንም በመቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ፡፡›› *(ማቴ. 27:3-5)*

‹‹ይሁዳ በግንባሩ ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ፤ አንጀቱም ተዘራገፈ፡፡›› *(የሐዋ ሥራ 1: 15-18)* የትኛዉ ነዉ ትክክለኛዉ የይሁዳ ሞት? አንድ ግለሰብ ሁለት ዓይነት አሟሟት ሊሞት ይችላልን?

3/ ስለዚህስ ሰዉ ኢየሱስ ምን አለ?

*ሀ)* ‹‹የሰዉ ልጅስ /ኢየሱስ/ ስለ እርሱ እንደተጻፈ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን የሰዉ ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት*!* ያ ሰዉ ባልተወለደ ይሻለዉ ነበር፡፡›› *(ማቴ፡ 26: 21-24)*

ለ) ‹‹ኢየሱስም ደግሞ ‹እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁ በሃጥአተችሁም ትሞታላቸሁ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም› አላቸው፡፡›› (ዮሐ. 8:21- 22) ከላይ የተጠቀሱት ሁለት አንቀፆች ይሁዳ በኢየሱስ ፋንታ እንደሚሞት የሚያስጠነቅቁ ናቸዉ፡፡

ሐ) በቱርክ ከተገኘዉ መጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርኣን በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ እንዳልተሰቀለ ይናገራል፡፡

1/ ‹‹እርሱም በሥጋዉ ወራት ከሞት ሊያድነዉ ወደሚችል፣ ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ፀሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት፡፡›› (ዕብራ. 5:7-8)

2/ ‹‹ሰይጣንም ወደ ኢየሩሳሌም ደግሞ ወሰደዉ፤ በመቅደስም ጫፍ ሊይ አቁሞ ‹ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፤ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዲትሰናከል በእጃቸዉ ያነሱሃል› ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፣ ከዚህ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለዉ፡፡›› (ሉቃስ *4:10-11)* ከክርስቲያኖች ይልቅ ሰይጣን የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ለኢየሱስ እንደተጻፈ ያውቃልን?

3/ ‹‹ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፤ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህንም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸዉ ያነሱሃል።›› *(መዝሙር 91፡10-16)* ይህ ትንቢት ለኢየሱስ የተነገረ መሆኑን ሰይጣን ሲናገር አይገርምም? አላህ ወደርሱ አነሳው ከሚለው የቅዱስ ቁርኣን አንቀጽ ጋር የሚጣጣም ነው።

***

## <u>የመልዕክቱ ማጠቃለያ</u>

ሚስጥረ ሥላሴ አሁን ያለውን መልክ ይዞ ለአምልኮ የበቃው ከ325 የኒቂያ ጉባኤና ከ381 የቁንስጥንጥኒያ ጉባኤ በኋላ መሆኑን የቤተ-ክርስቲያን መዛግብትና የዓለም ታሪኮች በሚገባ ያስታውሱናል። ጉባኤዎቹ የተካሄዱባቸውን ጊዜያት፣ ቦታዎቻቸውንና የጉባኤዎችን ተሳታፊዎች ጭምር በመዘርዘር ይዘክሩልናል። ስለሆነም ‹‹ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፤ በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ይመራል።›› *(ምሳሌ 16፡25)* ተብሏልና ወደ ጥንቱ እምነት እንመለስ።

1/ የኒቂያ ጉባኤተኛ ‹‹ክርስቶስ አምላክ አይደለም›› በሚለው በአሪዮስ መከራከሪያ አጀንዳ ላይ ተፋልሞ በፍጹም ክርስቶስ አምላክ ነው ብሎ በመደንገግ የሃይማኖት መግለጫ በማውጣት ተጠናቀቀ።

2/ የቆንስጣንጥኖሱም ጉባኤ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ብሎ አረፈ። የሥላሴም አንደ አካል ነው ብሎ በአንድ የድምጽ ብልጫ አጸደቀ። (ምንጭ፡- ከቃለ ሕይወት ቁጥር 15.1990 የተወሰደ) ‹‹እግዚአብሔር ሰውን ቅን አድርጎ መሥራቱን፣ ሰዎች ግን ዉስብስብ ዘዴ ቀየሱ።›› *(መክብብ 7፡ 29)* ታዲያ ከዉስብስብ ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ ሚስጥረ ሥላሴ አይደለምን? ስለዚህ ሥላሴ የሚለው ቃል ከኒቂያና ከቆንስጥንጥንያ ጉባኤዎች በኋላ የተፈበረከ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። አመጣጡንም ከኢንተርኔት ማወቅ ይቻላል። ‹Origin of Trinity› ብለው ጎግል ላይ ይፈልጉ!!!

ስለሆነም እውነተኛው አምላክ ማነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የ325 እና የ381 መንፈሳዊ ጉባኤዎችና ያወጡዋቸው መግለጫዎች አያስፈልጉም፤ ምክንያቱም ጌታችን አላህ መልዕክተኞችን በግልጽ ማስረጃ በመላኩ ማን በእውነት መመለክ እንዳለበት አስረድቶናልና። ማስረጃውም በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ይገኛል። ‹‹መልዕክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች ላክን፤ ሰዎችን በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን።›› *(አል-ሐዲድ 57፡25)*

3/ ‹‹ከእስልምና ሌላ ሃይማኖት የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከካሳሪዎቹ ነው።›› *(ሊ. ዒምራን 3፡85)*

እስላም ማለት ያላንዳች እምቢተኝነት ለአንድ ፈጣሪ እራስን ማስገዛት ወይም መታዘዝ ማለት ነው። ሙስሊም ማለት ደግሞ እራሱን ለፈጣሪ ያስገዛና ትዕዛዛቱን የፈፀመ ሰው ማለት ነው። ኢየሱስም ቢሆን ለአምላኩ ታዛዥ ወይም ሙስሊም ነው። እንዲህም ብሏል፡-

‹‹መልካም የሆነ አንድ ነው ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትዕዛዛትን ጠብቅ አለው።›› *(ማቴ 19፡17)* አዎን! ኢየሱስ የተናገረው ይህንን ነው እንጂ እኔ ሞቼልህ በሥጋዬና በደሜ ትፀድቃለህ አላለም።

አምላካችን አላህ በተከበረው ቃሉ ለመላው የመጽሐፉ ሰዎች (ለክርስቲያኖችና አይሁዶች) ቀጣዩን ግብዣ ያቀርብላቸዋል፡፡

‹‹*የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ!* በኛና በናንተ *መካከል* ትክክል *ወደሆነች ቃል* ኑ፤ *(እርሷም)* አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፣ እኛ *ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ* በላቸው፡፡›› (አል እምራን *3፡64)*

***

**ተፈጸመ**